# ኒያላ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር
# የተሻሻለ መመስረቻ ጽሁፍ (ረቂቅ)

ህዳር  2017 ዓም

# ማውጫ

ገፅ

መግቢያ፤ ........ 1
አንቀጽ አንድ፡
የማህበሩ መጠሪያ (ስም) ........ 2
አንቀጽ ሁለት፡
የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፣ ቅርንጫፎች እና ተቀጥላ ማኅበራት ........ 2
አንቀጽ ሦስት፡
የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ዝርዝር መግለጫ ........ 2
አንቀጽ አራት፡
የማህበሩ የንግድ አላማዎችና የስራ መስክ ........ 2
አንቀጽ አምስት፡
የማህበሩ ዋና ገንዘብ /ካፒታል/ ........ 3
አንቀጽ ስድስት፡
ስለአክሲዮኖች አይነት እና መደብ ........ 4
አንቀጽ ሰባት፡
የአክሲዮኖች አከፋፈልና ቀሪ ዋጋቸው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ስለሚኖር ኃላፊነት ........ 4
አንቀጽ ስምንት፡
ከአክሲዮን ይዞታ የሚመነጩ የባለአክሲዮኖች መብቶችና ግዴታዎች ........ 5
አንቀጽ ዘጠኝ፡
የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች መብትና ኃላፊነት ........ 5
አንቀጽ አስር፡
በመያዣ ወይም በአላባ ስለሚሰጡ አክሲዮኖች ........ 6
አንቀጽ አሥራ አንድ፡
የባለአክሲዮኖች መዝገብ ........ 6
አንቀጽ አሥራ ሁለት፡
አክሲዮኖችን ለሌላ ወገን ስለማስተላለፍ ........ 7
አንቀጽ አስራ ሶስት፡
የአክሲዮን ማኅበሩ የሥራ አመራር አካላት ........ 7
አንቀጽ አሥራ አራት፡
የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ........ 8

አንቀጽ አሥራ አምስት፡

የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር ....8

አንቀጽ አሥራ ስድስት፡

የጠቅላላ ጉባዔዎች የጥሪ ማስታወቂያ እና በባለአክሲዮን መዝገብ ስለመጻፍ ....10

አንቀጽ አሥራ ሰባት፡

ውክልና ....11

አንቀጽ አስራ ስምንት፡

የጥቅም ግጭት ....11

አንቀጽ አስራ ዘጠኝ፡

መደበኛና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ለማካሄድ ስለሚያስፈልገው ምልዓተ-ጉባዔ እና ውሳኔ የሚተላለፍበት ድምጽ ....11

19.1. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፡- ....11

19.2. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ፡- ....12

አንቀጽ ሃያ፡

የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔዎች ....12

አንቀጽ ሃያ አንድ፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ መሰየም እና የሥራ ዘመን ....13

አንቀጽ ሃያ ሁለት፡

የቦርድ አባላት ቁጥር ....14

አንቀጽ ሃያ ሶስት፡

ለአክሲዮን ማኀበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ ....14

አንቀጽ ሃያ አራት፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር ....14

አንቀጽ ሃያ አምስት፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ የስብሰባ ቦታ፣ አጠራር እና የአሰራር ደንብ ....16

አንቀጽ ሃያ ስድስት፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ....17

አንቀጽ ሃያ ሰባት፡

ዳይሬክተሮችን ስለመተካት ....17

አንቀጽ ሃያ ስምንት፡

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለማህበሩ ስላለባቸው ተጠያቂነት ....18

አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ፡

የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር ....18

አንቀጽ ሰላሳ፡

የውጭ ኦዲተር/ሮች ስያሜ፤ ኃላፊነትና ተግባር ....21

አንቀጽ ሰላሳ አንድ፡

የማኅበሩ ጸሐፊ ሹመት፤ ሥልጣንና ተግባር ........ 22

አንቀጽ ሰላሳ ሁለት፡

ስለአክሲዮን ማኅበሩ ሂሳብ አያያዝና ተዛማጅ ተግባራት ........ 22

ጠቅላላ ድንጋጌ ........ 22

አንቀጽ ሰላሳ ሶስት፡

የፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች ........ 22

አንቀጽ ሰላሳ አራት፡

የማኅበሩ የሂሳብ ዓመትና ሪፖርት ........ 23

አንቀጽ ሰላሳ አምስት፡

የሂሳብ ሠነዶችን እና ሪፖርቶችን ስለመስጠት ........ 23

አንቀጽ ሰላሳ ስድስት፡

በጥሬ ገንዘብ ስለሚያዙ ሂሳቦችና የመጠባበቂያ ገንዘብ ........ 23

አንቀጽ ሰላሳ ሰባት፡

በቸልተኝነት ወይም እምነት ማጉደል ምክንያት ለሚደርሱ ኪሣራዎች ........ 23

የሚሸፈኑባቸው መጠባበቂያዎች ........ 23

አንቀጽ ሰላሳ ስምንት፡

ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሳቦች ........ 24

አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ፡

የትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል ........ 24

አንቀጽ አርባ፡

ካፒታል በሚቀነስበት ጊዜ የሚደረግ የትርፍ ክፍፍል ዕገዳ ........ 24

አንቀጽ አርባ አንድ፡

ስለምዝገባና ሪፖርቶችን ይፋ ስለማድረግ ........ 25

አንቀጽ አርባ ሁለት፡

የአክሲዮን ማኅበሩን ለማፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች እና አግባብነት ያላቸው ሥነ-ሥርዓቶች ........ 25

አንቀጽ አርባ ሶስት፡

አክሲዮን ማኅበሩ በሥራ የሚቆይበት ጊዜ ........ 25

አንቀጽ አርባ አራት፡

ልዩ ልዩ ጉዳዮች ........ 26

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እንዲሁም የማህበሩ ጸሐፊ  ሥም እና ፊርማ፤ ........ 26

## ኒያላ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር

## የተሻሻለ መመስረቻ ጽሁፍ

**መግቢያ፤**

ኒያላ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር (ከዚህ በኃላ **"አክሲዮን ማኀበሩ"** እየተባለ የሚጠራው)፤የመድን ስራ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመቆጣጠር በወጣው የቀድሞው አዋጅ ቁጥር 86/1986 እና በ1952 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 166/1952 መሠረት አደራጆቹ የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅተው በወቅቱ በነበረው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት የክልል 14 መስተዳድር የውል ምዝገባ መመሪያ ተቋም ሚያዚያ 05 ቀን 1987 ዓ.ም አስመዝግበው ስራ ላይ እንዲውል አድርገው የነበረ ቢሆንም፤ የመመስረቻ ጽሁፉ በተለያየ ጊዜ እየተሻሻለ የቆየ እና እነዚህን በተለያየ ጊዜ የነበሩ ማሻሻያዎች በአንድ አጠቃሎ ማውጣት በማስፈለጉ፤

አክሲዮን ማህበሩ የአስተዳደር አካላትን ተግባራትና ኃላፊነት የሚወስን ዝርዝር የመተዳደሪያ ደንብ ያለው ቢሆንም፤በ1952 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 166/1952 በ2013 ዓ.ም አዲስ በወጣው የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 (ከዚህ በኃላ "የንግድ ሕግ" እየተባለ በሚጠራው) በመተካቱ፤ይህ የተሻሻለው አዲሱ የንግድ ሕግም ለአክሲዮን ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ እውቅና የማይሰጥ በመሆኑ እነዚህን የመተዳደሪያ ደንቡን ድንጋጌዎች በመመስረቻ ጽሁፉ ውስጥ ማጠቃለል በማስፈለጉ፤

በመመስረቻ ጽሁፉ ውስጥ የሚገኙ የሕግ ድንጋጌዎች፣ ቃላትና ሐረጎችን ከተሻሻለው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ማስተካከያ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የኒያላ ኢንሹራንስ ባለአክሲዮኖች (ከዚህ በኂላ **"ባለአክሲዮኖች"** ተብለን የምንጠራው) ህዳር 17 ቀን 2017 ዓ.ም ባደረግነው የ23ኛው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩን የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ /ከነማሻሻያዎቻቸው/ በአንድ ላይ በማጠቃለል እና በማሻሻል በንግድ ህግ አንቀጽ 400 (1) መሠረት ይህን የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሁፍ አጽድቀነዋል። ይህ ሰነድ የኒያላ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር የተሻሻለ መመሥረቻ ጽሁፍ ተብሎ ይጠራል። (በዚህ ሠነድ በነጠላ ቁጥር የተጠቀሰው አገባብነት ሲኖረው ለብዙም ያገለግላል። በወንድ ፆታ የተጠቀሰው አገባብነት ሲኖረው ለሴት ፆታም ያገለግላል።)

## አንቀጽ አንድ፡
## የማህበሩ መጠሪያ (ስም)

የማህበሩ መጠሪያ ወይም ስም “ ኒያላ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር ” ነው፡፡

## አንቀጽ ሁለት፡
## የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፣ ቅርንጫፎች እና ተቀጥላ ማኅበራት

2.1. የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ቦሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 04፣ የቤት ቁጥር 330 /ፕሮቴክሽን ሀውስ/ ሲሆን አድራሻው እንደ አስፈላጊነቱ ሊቀየር ይችላል፡፡

2.2. ማህበሩ እንደአስፈላጊነቱ ተገቢውን ፍቃድ ከሚመለከተው አካል ሲያገኝ በኢትዮጵያ ግዛትም ሆነ ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ ቅርንጫፎች፣ተቀጥላ ማኅበራትን እና ተጠሪ መስሪያ ቤቶች /ጽ/ቤቶች/ ሊከፍት ወይም ሊያቋቁም ይችላል፡፡

2.3. ይህ የመመስረቻ ፅሑፍ ሲጸድቅ በሥራ ላይ ያሉት አክሲዮን ማኅበሩ ቅርንጫፎች ዝርዝር አባሪ ሆኖ ተያይዟል፡፡

## አንቀጽ ሦስት፡
## የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ዝርዝር መግለጫ

ይህ መመስረቻ ጽሁፍ ሲሻሻል ያሉ የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የፈረሙት የአክሲዮን ብዛትና የከፈሉት የገንዘብ መጠን የፈረሙት አክሲዮን ብዛትና የከፈሉትን የአክሲዮን ዋጋ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ከዚህ የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ ጋር አባሪ ሆኗል፡፡

## አንቀጽ አራት፡
## የማህበሩ የንግድ አላማዎችና የስራ መስክ

አክሲዮን ማኅበሩ የሚከተሉት ዓላማዎች እና የሥራ መስኮች ይኖሩታል፡፡

4.1. የረጅም ጊዜ መድን ስራ መስራት፤

4.2. የጠቅላላ መድን ሥራ መስራት፤

4.3. በሸሪያ መርህ የሚሰጥ ኢንሹራንስ (ኢስላማዊ ኢንሹራንስ) መስራት፤

4.4. ማንኛውንም የመድንና የጠለፋ መድን ሥራዎችን በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያም ውጭ ማከናወን፤

4.5. አክሲዮን ማኅበሩ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከሌሎች የመድን ወይም የጠለፋ ዋስትና ተቋማት ጋር የጠለፋ መድን ሥራ መካፈል፤

4.6. ለሌሎች የመድንና የጠለፋ መድን ማኅበራት ወኪል ወይም ተጠሪ ሆኖ መሥራት፤

4.7. ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ተመሳሳይ ወይም ከላይ ከተጠቀሱት ሥራዎች ተጓዳኝ የሆኑትን ማንኛውንም ንግድ እንዲሁም ከኢንቨስትመንት ዓላማ ጋር የተገናኙ እና/ወይም የንግድ ዓላማውን ለማራመድ የሚረዱ የንግድ ሥራዎችን ማከናወን፤

4.8. በኢንቨስትመንት የማማከርና ሀብት የማስተዳደር አገልግሎቶችን መስጠት፤

4.9. በሪል እስቴት የድለላ አገልግሎት መስጠት፤

4.10. በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙና አክሲዮን ማሕበሩ ከፍተኛ የባለቤትነት ድርሻ ለያዘባቸው ድርጅቶች መረጃ የማጠናቀር አገልግሎት የመስጠት፤

4.11. ሕንፃ መገንባት፣ መሸጥ ወይም መግዛትና ማከራየት እንደዚሁም በሪል እስቴት ኢንቨስትመንት ውስጥ መሰማራት፤

4.12. አክሲዮን ማኅበሩ ከሚያራምደው የመድን ሥራ ዓይነት ጋር በተያያዘ ለመድን ወኪሎች እና ለመድን ደላሎች እገዛ ማድረግ፤

4.13. ንብረት በአደራ የማስቀመጥ ተግባር ማከናወን፤

4.14. የኢንቨስትመንት-መድን ቁርኝት አገልግሎት መስጠት፤

4.15. አክሲዮን ማኅበሩ ከሚያካሂዳቸው የመድን ሥራዎች ጋር በተያያዘ የአደጋ ሥጋት አስተዳደርና ጉዳት የማስተካከያ ምክር አገልግሎት መስጠት፤

4.16. አክሲዮን ማኅበሩ ከሚያካሂደው የመድን ሥራ ጋር በተያያዘ ለመድን ወኪሎችና ለመድን ደላላዎች መረጃዎችን የማጠናቀር አገልግሎት የመስጠት፤

4.17. አክሲዮን ማሕበሩ ከሚያካሂደው የመድን ሥራ ጋር በተያያዘ የባለሞተር ተሽከርካሪ ጥገናና ጉዳት ግምት አገልግሎት የሚሰጥበት ጋራጅ ማቋቋምና ማካሄድ፤

4.18. ሕግ በሚፈቅድለት የካፒታል ገበያ መስኮች መሰማራት፤

4.19. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም በተቆጣጣሪ አካል በተፈቀዱ ወይም ባልተከለከሉ ሌሎች የኢንቨስትመንት እና የንግድ ስራዎች ላይ መሳተፍ፡፡

## አንቀጽ አምስት፡
## የማህበሩ ዋና ገንዘብ /ካፒታል/

5.1. የማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ /ካፒታል/ ብር 1,733,726,000.00 /አንድ ቢሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሀያ ስድስት ሺ ብር/ ነው፡፡ የተፈረመ የማህበሩ ዋና ገንዘብ እያንዳንዳቸው ብር 1,000.00 (አንድ ሺ ብር) ዋጋ ባላቸው 1,733,726.00 (አንድ

ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺ ሰባት መቶ ሀያ ስድስት) በሆኑ መደበኛና የተመዘገቡ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው፡፡

5.2. ከተፈረመው የማህበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለው ብር 1,095,451,502.00 /አንድ ቢሊዮን ዘጠና አምስት ሚሊዮን አራት መቶ ሀምሳ አንድ ሺ አምስት መቶ ሁለት ብር/ ነው።

## አንቀጽ ስድስት፡
## ስለአክሲዮኖች አይነት እና መደብ

ማህበሩ ተመሣሣይ 1,000.00 (አንድ ሺ ብር) ዋጋ ያላቸው ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብ የሚከፈሉ አንድ አይነት እና እኩል የሆኑ፣ ልዩ መብት የማይሰጡና የተመዘገቡ መደበኛ አክሲዮኖች ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ ሰባት፡
## የአክሲዮኖች አከፋፈልና ቀሪ ዋጋቸው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ስለሚኖር ኃላፊነት

7.1. ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮን ለመግዛት በፈረሙ ጊዜ ቢያንስ የፈረሙትን አክሲዮኖች 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ያህል ወዲያውኑ መክፈል አለባቸው፡፡ ይህ ወዲያውኑ መከፈል የሚኖርበት የገንዘብ መጠን ከ25% (ሃያ አምስት በመቶ) በላይ እንዲሆን ካስፈለገ የአዲስ አክሲዮኖችን ሽያጭ በሚወስንበት ጊዜ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው መጠኑ ከ25% (ሃያ አምስት በመቶ) በላይ እንዲሆን ለመወሰን ይችላል፤

7.2. ተፈርሞ ያልተከፈለ ቀሪ የአክሲዮን ዋጋ የሚከፈልበት ጊዜ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰን ይሆናል፤

7.3. የአክሲዮን ማኅበሩ ነባር ባለአክሲዮኖች፣ ቀደም ሲል አክሲዮን ተላልፎላቸው የነበሩ ሰዎች እንዲሁም አክሲዮን ከማህበሩ ለመግዛት የፈረሙ አዲስ ባለአክሲዮኖች በተፈረሙ አክሲዮኖች ላይ ላልተከፈለው ቀሪ ገንዘብ ክፍያ ኃላፊነት አለባቸው፤

7.4. አክሲዮኖቹ የተሰጡት በአላባ ጥቅም እንደሆነ፤ ባለአላባው የአላባው ጊዜ መብት ሲያልቅ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ለመጠየቅ ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባልተከፈለ የአክሲዮን ገንዘብ ላይ ጥሪ ሲቀርብለት ቀሪውን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፤

7.5. መክፈል በሚገባቸው ጊዜ ውስጥ ያልከፈሉ ባለአክሲዮኖች 12% (አስራ ሁለት በመቶ) ወለድ ጨምረው ይከፍላሉ በተጨማሪም ድምፅ የመስጠት መብታቸውን ያጣሉ፤

7.6. ከላይ በአንቀጽ 7.5 የተቀሰው ቢኖርም ዋጋቸው ያልተከፈለ አክሲዮኖች ቀሪ ሂሳብ እንዲከፈል በደብዳቤ የ15 ቀን ጥሪ በማድረግ በተወሰነው ቀን ካልተከፈለ የዳይሬክተሮች

ቦርድ ቀሪ ያልተከፈሉ አክሲዮኖችን በተፃፈባቸው ዋጋ ለነባር ባለአክሲዮኖች ለመሸጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ስምንት፡
## ከአክሲዮን ይዞታ የሚመነጩ የባለአክሲዮኖች መብቶችና ግዴታዎች

አግባብ ያላቸው ሕጐችና ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አክሲዮኖች ለባለአክሲዮኑ የሚከተሉትን መብቶች ያሰጣሉ፡፡

8.1. ጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የመገኘት፣ የመሳተፍ እና ድምጽ የመስጠት፤

8.2. የአክሲዮን ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ የመመረጥ፤

8.3. በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚጸድቀውን የትርፍ ድርሻ በከፈሉት የአክሲዮን መጠን (የከፈለበት ጊዜ ታሳቢ ተደርጐ) ልክ የማግኘት፤

8.4. በሕግ መሠረት ድምጽ የመስጠት መብትን የሚያሳጡ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር በእያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምጽ የመስጠት መብት፤

8.5. ካፒታል ለመጨመር አዲስ አክሲዮኖች በሚወጡበት ጊዜ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን አስቀድሞ በያዛቸው የተከፈለባቸው አክሲዮኖች መጠን ልክ አዲስ አክሲዮን የመግዛት ቅድሚያ የማግኘት፤

8.6. ቃለ-ጉባኤዎችን እና ጠቅላላ ጉባኤዎች ላይ የተገኙ አባላትን ስም ዝርዝር የመመልከት መብት እንዲሁም የሀብትና ዕዳ ሚዛን(መግለጫ)፣ የትርፍና የኪሣራ መግለጫ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የኦዲተሮች ሪፖርቶችን ቅጅዎች የማግኘት ወይም የመውሰድ፤

8.7. አክሲዮን ማህበሩ በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት በሚፈርስበት ጊዜ ከሚገኘው የተጣራ የአክሲዮን ማኅበሩ ንብረት ለካፒታል ባስገባው መዋጮ መጠን ተሰልቶ ከተረፈው ንብረት ላይ ድርሻውን የማግኘት ናቸው፡፡

8.8. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና አግባብነት ባላቸው ሕጐችና ድንጋጌዎች መሠረት የሚመሩ ሆኖ፤ ባለአክሲዮኖች ለማህበሩ ዕዳ ወይም ግዴታ ተጠያቂ የሚሆኑት በስማቸው በያዟቸው አክሲዮኖች ዋጋ መጠን ልክ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ፡
## የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች መብትና ኃላፊነት

9.1. ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች አክሲዮን በጋራ መግዛት ይችላሉ፡፡ እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ የባለአክሲዮንነት መብታቸውን የሚጠቀሙት የጋራ ወኪል በመሾም ነው፤

9.2. የጋራ ወኪል ባልሾሙ ጊዜ ማህበሩ ለአንዱ ባለአክሲዮን የጋራ ባለቤት የሚሰጠው ማስታወቂያ ወይም መግለጫ ለቀሪዎቹ የአክሲዮኑ የጋራ ባለቤቶችም ጭምር እንደተሰጠ ይቆጠራል፤

9.3. የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች ከባለአክሲዮንነት ለሚመነጩ ኃላፊነቶች በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ናቸው፡፡

## አንቀጽ አስር፡
## በመያዣ ወይም በአላባ ስለሚሰጡ አክሲዮኖች

10.1. የተለየ ስምምነት በሌለ ጊዜ፤ አክሲዮኖቹ በመያዣ ወይም በአላባ ጥቅም የተሰጡ እንደሆነ በማኅበሩ ጉባዔዎች ድምፅ የመስጠት መብት የሚኖረው አክሲዮኑን በመያዣ የያዘው ወይም የአላባ ጥቅም ያለው ሰው ነው፤

10.2. ለነባር ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮን ለመግዛት በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ የተቀመጠው የቅድሚያ የመግዛት መብት የባለአክሲዮኑ ሆኖ ይቀጥላል፤

10.3. በመያዣ ለተሰጠ አክሲዮን የሚከፈል ቀሪ ገንዘብ መክፈል ያለበት ባለአክሲዮኑ ነው፡፡

## አንቀጽ አሥራ አንድ፡
## የባለአክሲዮኖች መዝገብ

11.1. አክሲዮን ማኅበሩ የባለአክሲዮኖችን መዝገብ መያዝ አለበት፡፡ መዝገቡ በአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት መያዝ ያለበት ሲሆን በወረቀት ሰነድ ወይም ለረዥም ዘመን በሚቆይ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ መያዝ ይችላል፤

11.2. መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የአክሲዮኖች ብዛትና መለያ ቁጥር፣ የተከፈለውንና ያልተከፈለውን ገንዘብ መጠን እንዲሁም ባለአክሲዮኖቹ የተመዘገቡበትን ቀን መያዝ አለበት፤

11.3. መዝገቡ ማንኛውም ባለአክሲዮን እና ማንኛውም በሕግ የተፈቀደለት ሰው ሊመለከተው እንዲችል ሆኖ በአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት ለረጅም ጊዜ በሚቆይ መልኩ በወረቀት ሠነድ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ተይዞ በመደበኛ የሥራ ሰዓታት ሁሉ ክፍት ሆኖ ይቀመጣል፤

11.4. ባለአክሲዮኖች እና ማንኛውም በሕግ የተፈቀደለት ሰው የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም የመዝገቡን ግልባጭ ወይም በአጭር የተውጣጣ ጽሑፍ እንዲሰጠው አክሲዮን ማኅበሩን መጠየቅ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሁለት፡
## አክሲዮኖችን ለሌላ ወገን ስለማስተላለፍ

12.1. የተመዘገቡ አክሲዮኖች ባለቤትነት የሚረጋገጠው የአክሲዮኖች መዝገብ በሚያመለክተው መሰረት ይሆናል፤

12.2. አክሲዮኖችን የማህበሩ ባለአክሲዮን ላልሆነ ሰው በሽያጭ ማስተላለፍ የሚቻለው ለማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ በማሳወቅ በቅድሚያ ፈቃድ ከተገኘ በኋላ ነው፤እንዲህ በሆነ ጊዜም ባለአክሲዮኖች ወይም አክሲዮን ማኅበሩ በቀደምትነት የመግዛት መብት ይኖራቸዋል። የአክሲዮን ማኅበሩ ወይም የባለአክሲዮኖች በቀዳሚነት አክሲዮኖችን የመግዛት መብት የሚፈፀመው የአክሲዮን ማኅበሩ  የውጭ ኦዲተሮች ስለአክሲዮን ማኅበሩ ባቀረቡት የመጨረሻው የበጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት ላይ ተመስርቶ በሚደረግ የአንድ አክሲዮን የመሸጫ ዋጋ ስሌት የገንዘብ መጠን ይሆናል፤

12.3. አክሲዮኖች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ ይኸው ሁኔታ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ መመዝገብ ያለበት ሲሆን በባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ካልተጻፈ በስተቀር የአክሲዮን መብት ለተላለፈለት ሰው የተሟላ ሆኖ አይቆጠርም፤ የአክሲዮን ዝውውርም ዋጋ አይኖረውም፤

12.4. አንድ ባለአክሲዮን በሚሞትበት ጊዜ አክሲዮን ማኅበሩ በባለአክሲዮንነት የሚቀበላቸው በፍርድ ቤት አክሲዮኑ እንዲተላለፍላቸው የተወሰነላቸውን ነው፤

12.5. አክሲዮኖችን በጋራ ከያዙ ባለአክሲዮኖች መካከል አንዱ ቢሞት የሟች የአክሲዮን ድርሻ ላይ መብት የሚኖራቸው በፍርድ ቤት የሟቹ ህጋዊ ወራሽ /ወራሾች/ የሆኑት ናቸው።

## አንቀጽ አስራ ሶስት፡
## የአክሲዮን ማኅበሩ የሥራ አመራር አካላት

የአክሲዮን ማኅበሩ አመራር አካላት የሚከተሉት ናቸው።

13.1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፣

13.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ፣

13.3. ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣

13.4. የውጭ ኦዲተር/ሮች

13.5. የማኅበሩ ፀሐፊ ናቸው።

## አንቀጽ አሥራ አራት፡
## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

14.1. የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ዓይነቶች መደበኛ ወይም አስቸኳይ ይሆናሉ፤

14.2. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፣ የበጀት ዓመቱ በተዘጋ በስድስት ወራት ውስጥ በዓመት አንድ ጊዜ መደረግ አለበት፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔዎች ሊደረጉ ይችላሉ፤

14.3. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የሚያደርጉት እንደነገሩ ሁኔታ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ የውጭ ኦዲተር/ሮች፣ የሒሳብ አጣሪዎች፣ ፍርድ ቤት ወይንም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ናቸው፤

14.4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14.3 ሥር የተመለከተው ቢኖርም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግስት አካል ጉዳዩ አንገብጋቢ ሆኖ ሲያገኘው እና በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 14.2 መሠረት ስብሰባ መጥራት የማይቻል ወይም ረጅም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ማንኛውም ሰው ጥያቄ ወይም በራሱ ተነሳሽነት ጉባዔ ሊጠራ ይችላል፤ ሆኖም ጉባዔው እንዲጠራ ጥያቄ የቀረበው የአክሲዮን ማሕበሩ ዋና ገንዘብ አሥር በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ከሆነ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግሥት አካል ጉባዔ የመጥራት ግዴታ አለበት፤

14.5. ከአክሲዮን ማኅበሩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አምስት በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡና ፍርድ ቤቱ ጥያቄው ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሰበሰብ ጥሪ የሚያደርግና አጀንዳ የሚያዘጋጅ ተወካይ ሊሰይም ይችላል፤

14.6. በጠቅላላ ጉባዔ ላይ ባለአክሲዮኖች በአካል በመገኘት ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም ሁሉም ባለአክሲዮኖች የተስማሙ እንደሆነ ስብሰባ ማድረግ ሳያስፈልግ ለውሳኔ በቀረበ ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመግለጽ ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ አሥራ አምስት፡
## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

15.1. ጠቅላላ ጉባዔ የአክሲዮን ማኅበሩ የበላይ አካል ነው፤

15.2. የባለአክሲዮኖች የተለያዩ ዓይነት ጠቅላላ ጉባዔዎች በንግድ ሕግና በዚህ የአክሲዮን ማኅበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ በተወሰነው መሠረት ይካሄዳል፤

15.3. በንግድ ሕግና አግባብነት ባላቸው የመድን ሥራ ሕጐች ውስጥ የተደነገገው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፡-

15.3.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ይሾማል፣ ይሽራል፣ ክፍያቸውንም ይወስናል፤

15.3.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ይሾማል፣ ይሽራል፣ ክፍያቸውንም ይወስናል፤

15.3.3. የአክሲዮን ማኅበሩን የሀብትና ዕዳ ሚዛን መግለጫ፤ የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ መግለጫ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት፣ የኦዲተሮችን ሪፖርት አድምጦ የማሻሻል ወይም የማጽደቅ፣ ወይም ያለመቀበል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትርፍ አመዳደብ እና አከፋፈል እንዲሁም በአጠቃላይ ያለፈውን የሂሳብ ዓመት ማጠቃለያ የተመለከቱ የሂሳብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያስተላልፋል፤

15.3.4. የአክሲዮን ማኅበሩን የውጭ ኦዲተሮች ይሰይማል፣ ይሽራል፣ የሥራ ጊዜያቸውንና ክፍያቸውንም ይወስናል፤

15.3.5. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲወስንባቸው ተለይተው ከተቀመጡት ውጭ ያሉ ጉዳዮችን ጠቅላላ ጉባዔው ይወስናል፡፡

15.4. አግባብነት ባላቸው ሕጐች እና በንግድ ሕግ ውስጥ የተደነገገው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፡፡

15.4.1. የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ ማሻሻያዎችን ያደርጋል፤

15.4.2. . የአክሲዮን ማኅበሩን ዓላማዎች ያሻሽላል፤

15.4.3. . የአክሲዮን ማኅበሩን ዋና ካፒታል ይቀንሳል ወይም ይጨምራል፤

15.4.4. . አክሲዮን ማኅበሩ እንዲፈርስና ሂሳቡም እንዲጣራ ይወስናል፤

15.4.5. . አክሲዮን ማኅበሩ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ሌላ አክሲዮን ማኅበር ወይንም የፋይናንስ ተቋም ወይንም ድርጅት ጋር እንዲጠቃለል፣ ከሌላ መድን ሰጪ ወይንም የፋይናንስ ተቋም ወይንም ድርጅት ጋር እንዲዋሀድ ወይም እንዲከፋፈል ሊወስን ይችላል፡፡

15.5. ለጉባዔው ዓይነትና የአጀንዳ ነጥብ እና በሕግ የሚጠየቀው ምልዓተ-ጉባዔ እንደተጠበቀ ሆኖ በጠቅላላ ጉባዔ የተላለፉ ውሳኔዎች በሁሉም ባለአክሲዮኖች፣ ወኪል ሰይመው

በጉባኤ ባልተገኙት ባለአክሲዮኖች፣ በሀሳብ በተለዩት፣ በውሳኔው ባልተስማሙ፣ ድምጽ ባልሰጡ ወይም ለመስጠት በማይችሉ ባለአክሲዮኖች ላይ ጭምር ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፤

15.6. ከላይ የተደነገገው ቢኖርም ባለአክሲዮኑ ራሱ ካልተስማማ በስተቀር ባለአክሲዮን በመሆኑ ምክንያት ሊያገኝ የሚገባውን መሠረታዊ መብት ጠቅላላ ጉባዔው ሊነፍገው አይችልም።

## አንቀጽ አሥራ ስድስት፡
## የጠቅላላ ጉባዔዎች የጥሪ ማስታወቂያ እና በባለአክሲዮን መዝገብ ስለመጻፍ

16.1. ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት በሚያስፈልግበት ጊዜ የስብሰባው ጥሪ ከስብሰባው ዕለት 24 (ሃያ አራት) ቀናት አስቀድሞ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይንም በአክሲዮን ማኅበሩ ወጪ በተመዘገበ ደብዳቤ ወይም የኢሜይል አድራሻ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊጠራ ይችላል፤

16.2. በመጀመሪያ ጥሪ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በምልዓተ-ጉባኤ አለመሟላት ሊካሄድ ካልቻለ ሁለተኛው ጥሪ የመጀመሪያው የጉባኤ ጥሪ በተፈጸመበት ሁኔታ እና ጊዜ ይጠራል፤

16.3. አስቸኳይ ጉባኤ አስፈላጊ ምልዓተ-ጉባኤ ባለመሟላቱ ምክንያት ሳይሰበሰብ የቀረ እንደሆነ ሁለተኛው ጉባኤ የመጀመሪያው ጉባኤ እንዲካሄድ ከተቀጠረበት ጀምሮ በሚቆጠር አንድ ሣምንት ውስጥ መጠራት አለበት። ሁለተኛው ጉባኤም ምልዓተ-ጉባኤ ሳይሟላ በመቅረቱ ምክንያት ሳይካሄድ የቀረ እንደሆነ ሦስተኛው ጉባኤ ሁለተኛው ጉባኤ እንዲካሄድ ከተቆጠረበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ የአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መጠራት አለበት፤

16.4. የጥሪ ማስታወቂያው በፖስታ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚተላለፍ ቢሆንም ስብሰባውን በሚጠራው አካል ውሳኔ መሠረት ጥሪው በተጨማሪ በጋዜጣ ሊደረግ ይችላል፤

16.5. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 16.1 እና 16.4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሌላ ማስታወቂያ ለባለአክሲዮኑ የሚተላለፍለት በአስመዘገበው አድራሻ መሠረት እንደአመቺነቱ በመልዕክተኛ፣ በፖስታ፣ በፋክስ፣ በኢሜል፣ በስልክ የጽሑፍ መልዕክት ወይም በሬዲዮ ወይም በጋዜጣ ሊሆን ይችላል፤

16.6. ማንኛውም የአክሲዮን ባለሀብት በባለአክሲዮኖች መዝገብ ውስጥ መጻፍ የሚችለው ጠቅላላ ጉባዔው ከሚደረግበት ቀን 3 (ሶስት) የሥራ ቀናት አስቀድሞ ነው፤ ይህ ሁኔታም የጥሪ ማስታወቂያው ላይ ይገለጻል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሰባት፡
## ውክልና

17.1. የውክልና ሠነዶች ጠቅላላ ጉባዔ ከሚደረግበት ዕለት ቢያንስ ሦስት ቀን አስቀድሞ ለአክሲዮን ማኅበሩ ዋና መ/ቤት መቅረብ አለባቸው፤

17.2. በጉባዔው ላይ ለመገኘት የሚያስችል የውክልና ይዘት፣ ተሞልተው የሚላኩበት የጊዜ ገደብና ቦታው በዳይሬክተሮች ቦርድ ተወስኖ በጥሪው ማስታወቂያ ላይ መገለጽ አለበት፤

17.3. አንድ ባለአክሲዮን የአክሲዮን ማኅበሩ ባለአክሲዮን በሆነ ወይም ባልሆነ ሰው ሊወከል ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስምንት፡
## የጥቅም ግጭት

18.1. በራሱ ስም ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገንን ወክሎ በጉባዔ ላይ የሚገኝ ተሳታፊ ከአክሲዮን ማኅበሩ ጥቅሞች ጋር የሚጋጭ ጥቅም ያለው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ተሳታፊው በቀረበው ጉዳይ ላይ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም፤

18.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የራሳቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በሚመለከት ውሳኔ ላይ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፤

18.3. ምልዓተ-ጉባዔ በሚሰላበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ መሠረት ድምፅ የመስጠት መብት የተነፈጋቸው አክሲዮኖች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ፡
## መደበኛና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ለማካሄድ ስለሚያስፈልገው ምልዓተ-ጉባዔ እና ውሳኔ የሚተላለፍበት ድምጽ

**19.1. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፡-**

19.1.1. በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የመጀመሪያ ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ከሚሰጡ የአክሲዮን ማኅበሩ አክሲዮኖች ቢያንስ አንድ አራተኛ (1/4) የያዙ ባለአክሲዮኖች ራሳቸው ወይም እንደራሴዎቻቸው መገኘት አለባቸው፤

19.1.2. በሁለተኛው ጥሪ የተወከሉት ድምጽ የመስጠት መብት የሚሰጡት አክሲዮኖች ቁጥር የትኛውንም ያህል ቢሆን ጉባዔው ስብሰባውን ለማካሄድና ውሳኔ ለማስተላለፍ ይችላል፤

19.1.3. ጉባዔው ላይ ድምጽ ተአቅቦዎችን እና ባዶ ድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ከግምት ውጭ በማድረግ በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የሚጸድቁት በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡

**19.2. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ፡-**

19.2.1. የአክሲዮን ማኅበሩ ዜግነት እንዲለወጥ የሚያደርጉ ወይም በነባር አክሲዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመጨመር የአክሲዮን ማኅበሩን ካፒታል ለማሳደግ የሚጠይቁ ውሳኔዎች ሁሉ ዋጋ ሊኖራቸው የሚችለው ድምጽ ለመስጠት መብት ያላቸውን አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች በአስቸኳይ ጉባዔው ላይ ተገኝተው ወይም ተወክለው በሙሉ ድምፅ ሲስማሙበት ብቻ ይሆናል፤

19.2.2. በማንኛውም አስቸኳይ ጉባኤ ላይ ውሳኔዎች በሁለት ሶስተኛ (2/3ኛ) አብላጫ ድምጽ የሚጸድቁ ሆኖ በሚከተለው መሠረት አፈጻጸሙ ይወሰናል፡፡

19.2.2.1. ለድምጽ ብልጫው አቆጣጠር ስሌት ድምጽ ያልሰጡም ሆነ ድምጽ ያልተጻፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ግምት ውስጥ አይገቡም፤

19.2.2.2. በመጀመሪያ ጉባዔ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ከአንድ ሶስተኛ (1/3) ያላነሱትን የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወከሉ፤

19.2.2.3. በሁለተኛው ጉባዔ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው የተፈረሙ አክሲዮኖች ከአንድ አራተኛ (1/4) ያላነሱ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖችን የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወክሉ፤

19.2.2.4. በሦስተኛው ጉባኤ የወከሉት ድምጽ የመስጠት መብት የሚሰጡት አክሲዮኖች ቁጥር የትኛውንም ያህል ቢሆን ጉባዔው ስብሰባውን ለማካሄድና ውሳኔ ለማስተላለፍ ይችላል፡፡

19.2.3. ሕግንና ይህን የመመሥረቻ ጽሑፍ በመተላለፍ በመደበኛም ሆነ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በተሰጡ ውሳኔዎች ጥቅሙ የተጐዳ ሰው፤ ውሳኔዎቹ ከተሰጡበት ቀን ጀምሮ በዘጠና (90) ተከታታይ ቀናት ውስጥ መቃወሚያ ሊያቀርብባቸው ይችላል፤

19.2.4. የአንድ ጉባዔ ውሳኔ እንዲሻር ወይም እንዲሰረዝ የሚቀርበው መቃወሚያ ላይ የንግድ ሕግ አንቀጽ 391 ንዑስ አንቀጽ (2-7) ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ ሃያ፡
## የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔዎች

20.1. በጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶች በቃለ-ጉባዔ መያዝ አለባቸው፡፡ ቃለ-ጉባዔዎች በስብሰባው ላይ በተገኙት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና በአክሲዮን ማህበሩ ፀሐፊ ይፈረማሉ፤

20.2. ቃለ-ጉባዔ ወደ መዝገብ በትክክል ስለመገልበጡ በአክሲዮን ማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በሌሎች ሁለት የቦርድ አባላት መረጋገጥ አለበት፤

20.3. የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔዎች በተለይ ከዚህ በታች የመለከቱትን ጉዳዮች መያዝ አለባቸው፡፡

20.3.1. የጉባዔውን ጥሪ አደራረግ፤

20.3.2. የስብሰባውን ቦታና ቀን፤

20.3.3. አጀንዳዎቹን፤

20.3.4. በጉባዔው የተገኙ የቦርድ አባላትን ስም፤

20.3.5. በስብሰባው ላይ የተገኙ አክሲዮኖችን ብዛትና የምልዓተ-ጉባዔውን ቁጥር፤

20.3.6. ለጉባዔው የቀረቡትን ሠነዶች፤

20.3.7. የውይይቱን አጭር ማጠቃለያ፤

20.3.8. የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና

20.3.9. ጉባዔው ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች፡፡

## አንቀጽ ሃያ አንድ፡
## የዳይሬክተሮች ቦርድ መሰየም እና የሥራ ዘመን

21.1. አክሲዮን ማኅበሩ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በሚመረጡ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል፤

21.2. ቦርዱ ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ከዳይሬክተሮች አባላት መካከል መርጦ ይሠይማል፤

21.3. የአክሲዮን ማኅበሩ ፀሐፊ የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤

21.4. የዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን ሦስት (3) ዓመት ነው፤ዳይሬክተሮቹ በየሶስት (3) ዓመቱ ይመረጣሉ፤

21.5. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥራ ተከታታይነት እንዲኖረው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን በየምርጫው ለሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን ካገለገሉ ነባር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ውስጥ ቢበዛ አንድ ሦስተኛው (1/3) ለሦስተኛ የሥራ-ዘመን እንደገና መመረጥ ይችላሉ፤

21.6. በአንቀጽ 21.5 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ከስድስት ተከታታይ ዓመታት በላይ በዳይሬክተርነት ማገልገል አይችልም፤ሆኖም የዳይሬክተሩ አገልግሎት ካበቃ ከስድስት (6) ዓመታት በኋላ እንደገና መመረጥ ይችላል፤

21.7. ጠቅላላ ጉባዔው በሕጉ እና በዚህ መመሥረቻ ጹሑፍ በተገለፀው መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በማናቸውም ጊዜ የማሰናበት ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የሦስት (3) ዓመት የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት ከ50% በላይ ዳይሬክተሮች ሲጓደሉ አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ጠቅላላ ጉባዔውን ሊጠይቅ ይችላል፤

21.8. በማገልገል ላይ ያሉት ዳይሬክተሮች ሲለቁ አዲስ ለተመረጡት ዳይሬክተሮች ሥራቸውን ማስተላለፍ የሚችሉት አዲስ ተመራጭ ዳይሬክተሮች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ካገኙ በኋላ ነው፤

21.9. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አዲስ የተመረጡ ዳይሬክተሮችን ሹመት በጽሑፍ እስኪያጸድቅ ድረስ የነባር ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን ሳይቋረጥ ይቀጥላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሁለት፡
## የቦርድ አባላት ቁጥር

አክሲዮን ማኅበሩ ዘጠኝ (9) የቦርድ አባላት /ዳይሬክተሮች/ ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሶስት፡
## ለአክሲዮን ማኅበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ

23.1. አክሲዮን ማኅበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 311 መሠረት ይይዛል፤

23.2. ባለአክሲዮኖች እና ሕግ የሚፈቅድላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተወካዮች መዝገቡን በነጻ ለማየት ይችላሉ፤ ባለአክሲዮን ያልሆኑ ሰዎች ለዚሁ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም መዝገቡን የማየት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ ሃያ አራት፡
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር

24.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ አግባብነት ባላቸው ሕጎች፣ በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የተሰጠ ወይም የሚሰጥ ተግባርና ሥልጣን ይኖረዋል፤

24.2. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ለሌላ አካል በሕግ ተለይቶ የተሰጠ ካልሆነ በስተቀር ለአክሲዮን ማኅበሩ የተሰጡ ሥልጣኖች ሁሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣኖች ይሆናሉ፤

24.3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 24.1 የተጠቀሰው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፡፡

24.3.1. የአክሲዮን ማህበሩን ሥራ አመራር ይቆጣጠራል፤

24.3.2. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያስተላለፉቸውን መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተከታትሎ ተግባራዊ ያደርጋል፤

24.3.3. የአክሲዮን ማኅበሩን ዋና ሥራ አስፈፃሚ መርጦ ይሾማል፣ ያሰናብታል፣ የቅጥር ሁኔታና ዘመን እንዲሁም ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ይወስናል፤

24.3.4. የዋና ሥራ አስፈፃሚ ምክትል የሆኑ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች /ሲኒየር ኤክስኪዩቲቭ ኦፊሰሮች/ የውስጥ ኦዲት ኃላፊና የሪስክና ኮምፕሊያንስ ኃላፊን በዋና ሥራ አስፈፃሚ ተመርጠው ሲቀርቡለት ሹመታቸውን ያጸድቃል፤

24.3.5. የአክሲዮን ማህበሩን ጸሐፊ ቅጥርና ስንብት በዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲቀርብለት ያጸድቃል፤

24.3.6. የአክሲዮን ማኅበሩን ስትራቴጂዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ሲስተሞችንና ዓመታዊ ዕቅድና በጀት እንዲሁም ድርጅታዊ መዋቅርና የደመወዝ ስኬል /እርከን/ በዋና ሥራ አስፈፃሚው ተዘጋጅተው ሲቀርቡለት በአግባቡ አጢኖ ውሳኔ ይሠጣል፤

24.3.7. የአክሲዮን ማህበሩ ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

24.3.8. የኢትዮጵያ ንግድ ሕግና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች በሚጠይቁት መሠረት የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያዘጋጃል፣ ይጠራል፣ ያካሂዳል፤

24.3.9. ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የዓመቱን የሥራ ክንውን ሪፖርት ከሂሳብ መግለጫዎች ጋር ያቀርባል፤

24.3.10. የሃብትና ዕዳ ሚዛን የትርፍና የኪሳራ ሂሳብ መግለጫና የዳይሬክተሮች ሪፖርትን ለውጭ ኦዲተር/ሮች አስቀድሞ ይሰጣል፣ ያቀርባል፤

24.3.11. ከኢትዮጵያ ውጭ ስለሚከፈቱ ቅርንጫፎች ውሳኔ ይሰጣል፤

24.3.12. በዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚቀርቡለትን የኢንቨስትመንትና የቋሚ ንብረት ግዥ ጥያቄዎች ያጸድቃል፤

24.3.13. አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ማናቸውንም ምክረ ሃሳቦች ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

24.3.14. አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ተለይተው ለሚታወቁ ጉዳዮች ብቻ የዳይሬክተሮች ቦርድ ለቦርዱ ሰብሳቢ እና/ወይም ለዋና ሥራ አስፈፃሚ የውክልና ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፤

24.3.15. የዳይሬክተሮች ቦርድ ከላይ ከተጠቀሱት ስልጣኖች በተጨማሪ የማይንቀሳቀሱ ወይም የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን የመግዛት፣ የመሸጥ እና የመለወጥ ጉዳዮች ላይ

የመወሰን ሥልጣን አለው። ቦርዱ ይህን ሥልጣኑን በቃለ-ጉባዔ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል፤

24.3.16. የዳይሬክተሮች ቦርድ የአክሲዮን ማኅበሩን የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ቋሚ ንብረቶች በዋስትና በማስያዝ ለአክሲዮን ማኅበሩ ጥቅም ብድር መበደር ይችላል። ቦርዱ ይህን ሥልጣኑን በቃለ-ጉባዔ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል፤

24.3.17. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ብድሮችንና ሌሎች ተሰብሳቢ ክፍያዎችን መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ መርሆዎችን በመከተል ከሂሳብ መዝገብ ላይ ሊሰርዝ ይችላል፤ እንዲሁም አገልግሎት መስጠት የማይችሉትን ቋሚ ንብረቶች ማስወገድ ወይም ከመዝገብ ላይ መሰረዝ ይችላል። ቦርዱ ይህን ሥልጣኑን በቃለ-ጉባዔ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል፤

24.3.18. ቦርዱ የአክሲዮን ማኅበሩን የአክሲዮኖች ግዢ እና ሽያጭ አገልግሎቶች እና ሌሎች የገንዘብ ሠነዶችን በካፒታል ገበያ ላይ አገልግሎት መስጠትን እንዲሁም በካፒታል ገበያ ላይ ያሉ ሌሎች ተሳትፎዎችን ይወስናል፤

## አንቀጽ ሃያ አምስት፡
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ የስብሰባ ቦታ፣ አጠራር እና የአሰራር ደንብ

25.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እና ም/ሰብሳቢ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይመረጣሉ፤

25.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢው የቦርድ ስብሰባ የመጥራት ሥልጣን ይኖረዋል። የዳይሬክተሮች ቦርድ በአክሲዮን ማኅበሩ ዋና ጽ/ቤት ወይም ሰብሳቢው በሚመርጠው በሌላ ቦታ ቢያንስ በወር አንድ (1) ጊዜ ይሰበሰባል። ከዚህም ሌላ የአክሲዮን ማኅበሩ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በሚያስፈልገው መጠን ተጨማሪ ስብሰባዎች ሊያካሂድ ይችላል፤

25.3. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው የቦርድ ስብሰባዎችን ሁሉ በሰብሳቢነት ያካሂዳል፤ ነገር ግን ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ ስብሰባው በሚሰየም ማናቸውም የቦርድ አባል/ዳይሬክተር ይመራል፤

25.4. የዳይሬክተሮች ቦርድ የአክሲዮን ማኅበሩን መመሥረቻ ጽሑፍና የንግድ ሕጉን መሠረት በማድረግ የራሱን የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ደንብ ማዘጋጀት ይችላል።

## አንቀጽ ሃያ ስድስት፡
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ

26.1. ከጠቅላላው የዳይሬክተሮች ቁጥር 51% (ሃምሳ አንድ በመቶ) የሚሆኑት በስብሰባው ላይ በራሳቸው ወይም በወኪላቸው ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ካልተገኙ በስተቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም። ውሳኔ የሚተላለፈው በድምጽ ብልጫ ነው። ማንኛውም ዳይሬክተር ወይም ተወካይ ድምጽ የመስጠት መብት ይኖረዋል። ድምጽ እኩል ለእኩል በሚከፈልበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፤

26.2. በቦርድ ስብሰባ ለመገኘት የማይችል ዳይሬክተር የሚወከለው በሌላ ዳይሬክተር ብቻ ይሆናል፤ አንድ ዳይሬክተር ሊወክል የሚችለው አንድ ሌላ ዳይሬክተርን ብቻ ነው፤

26.3. የቦርድ ውሳኔዎች በቃለ-ጉባዔ ተይዘው በስብሰባው ላይ በተገኙ ዳይሬክተሮች እና በማኅበሩ ጸሐፊ ይፈረማሉ። ቃለ-ጉባዔዎች በመዝገብ ይቀመጣሉ፤

26.4. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለማድረግ ይቻላል፤

26.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን በሚሰጥበት ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ባለሞያዎችን ሊያማክር ይችላል፤

26.6. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና ሲጠየቅ በዳይሬክተሮች ቦርድ የፀደቀው ማንኛውም የውሳኔ ቅጂዎች በሰብሳቢው እና በማኅበሩ ጸሐፊ እየተረጋገጡ መፈረም አለባቸው።

## አንቀጽ ሃያ ሰባት፡
## ዳይሬክተሮችን ስለመተካት

27.1. የዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 21.1 ድንጋጌ ቢኖርም፣ በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች በአንቀጽ 27.3 ላይ በተመለከቱት እና በማናቸውም ምክንያቶች ከቦርድ አባልነት የለቀቁ ወይም የተገለሉ እንደሆነ ያሉት ዳይሬክተሮች ለቀሪው የሹመት ጊዜ የሚተኩ ሌሎች ዳይሬክተሮችን አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት መሰየም ይችላሉ፤

27.2. የቦርድ አባላት በማናቸውም ጊዜ ቁጥራቸው ከ50% በታች የቀነሰ እንደሆነ የቀሩት አባላት የጐደሉትን ለማሾም አባላቱ ከጐደሉበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ጠቅላላ ጉባዔውን መጥራት አለባቸው፤ በጐደሉት አባላት ምትክ ሹመት እስኪደረግ ድረስ የቀሩት አባላት አክሲዮን ማኅበሩን ያስተዳድራሉ፤

27.3. በሚከተሉት ምክንያቶች አንድ ዳይሬክተር ከቦርድ አባልነቱ ሊገለል ይችላል፡-

27.3.1. ዳይሬክተሩ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ሲከስር ወይም ዕዳውን መክፈል ሲሳነው ወይም በዕዳው ምክንያት ሲዋሀድ፣

27.3.2. የአዕምሮ ቀውስ ሲደርስበት፣

27.3.3. በወንጀል ተከሶ ሲፈረድበት፣

27.3.4. ዳይሬክተሩ እያወቀ ከአክሲዮን ማኅበሩ ጋር የጥቅም ግጭት የሚፈጥሩ ተግባራት ላይ ሲሰማራ፣

27.3.5. ዳይሬክተሩ የአክሲዮን ማኅበሩን ጥቅም ለማስጠበቅ እርምጃ መውሰድ ሲሳነው፣

27.3.6. ቦርዱ በስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ እና በሥነ-ምግባር ደንብ ውስጥ በደነገገው ሌላ ምክንያት፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስምንት፡
## የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለማህበሩ ስላለባቸው ተጠያቂነት

28.1. አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በሕጉ፣ በመመሥረቻ ጽሑፍና በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ የተጣለበትን ኃላፊነት በሕጋዊ መንገድ በሚያከናውንበት ጊዜ ለሚከሰቱ ዕዳዎች በግል ተጠያቂ አይሆንም፡፡ ዳይሬክተሩ በቸልተኝነት ወይም ኃላፊነቱን በማጉደል ለሠራቸው ሥራዎች ግን ከኃላፊነት ነጻ አይሆንም፡፡

28.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በተገቢው ጥንቃቄና ትጋት ስለመስራታቸው የማስረዳት ሸክም አለባቸው፤

28.3. አክሲዮን ማኅበሩ ለቦርድ አባላቱ የሙያ ዋስትና ኢንሹራንስ ሊገባላቸው ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ፡
## የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር

29.1. አክሲዮን ማኅበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይኖረዋል፡፡ የዋና ሥራ አስፈፃሚው ተጠሪነት ለቦርድ ሆኖ፤ ደመወዙና ጥቅማ ጥቅሙም በቦርዱ ይወሰናል፤

29.2. የአክሲዮን ማኅበሩን ጠቅላላ የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል፤ይቆጣጠራል፡፡ የአክሲዮን ማሕበሩ ዋና ሥራ አስፈፃሚና ከፍተኛ ተጠሪ በመሆን የአክሲዮን ማሕበሩን አስተዳደር በበላይነት ለመምራት አጠቃላይ ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፤

29.3. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት አክሲዮን ማህበሩን ይወክላል፤

29.4. አግባብነት ባላቸው ሕጐች ለአክሲዮን ማኅበሩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የተሰጠው ሥልጣን፣ ተግባር፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

29.4.1. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ የተመለከቱትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በአክሲዮን ማኅበሩ ስም እና አክሲዮን ማኅበሩን ወክሎ ይሠራል፤

29.4.2. በዓለም አቀፍ እና በሀገር ውስጥ በሚያካሂዳቸው ሥራዎች ምክንያት አክሲዮን ማኅበሩን በሦስተኛ ወገኖች፣ በመንግሥት፣ በግል ድርጅቶችና በሌሎች የገንዘብ ተቋማት ዘንድ ይወክላል፤

29.4.3. ቦርዱን በማስፈቀድ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በዋስትና በማስያዝ ብድር ይጠይቃል፣ ይበደራል፣ ለታለመለት ሥራ ይውላል፤

29.4.4. በአክሲዮን ማኅበሩ ስም በማኛውም ባንክና በማንኛውም ሕግ በፈቀደላቸው ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣ ይዘጋል፤

29.4.5. ለአክሲዮን ማኅበሩ ሥራ እንቅስቃሴ ከሚያስፈልገው በላይ ያለን ገንዘብ የቦርድ ፈቃድ ሳያስፈልገው በባንክ የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ወይንም ተመሳሳይነት ባለው መስክ ኢንቨስት ለማድረግ ይችላል፤

29.4.6. የአክሲዮን ማኅበሩ ባለድርሻ በሆነባቸው እና በሚሆንባቸው ተቋማት ውስጥ በመመሥረቻ ፅሑፍ ላይ ይፈርማል፣ በጠቅለላ ጉባኤዎች ላይ በመገኘት በአክሲዮን ማኅበሩ ስም ድምፅ ይሠጣል፣ በቃለ-ጉባኤዎቹም ላይ ይፈርማል፤

29.4.7. እንደአስፈላጊነቱ በአክሲዮን ማኅበሩ ስም የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ይከራያል፣ የአክሲዮን ማኅበሩን ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያከራያል፣ አክሲዮን ማኅበሩን በመወከል የኪራይ ውሎችን ወይም ስምምነቶችን ይፈርማል፤

29.4.8. ቦርዱ በፈቀደው ወይንም ባፀደቀው ፖሊሲ መሠረት በአክሲዮን ማኅበሩ ስም የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ያስተላልፋል፤

29.4.9. የኢንሹራንስ ውሎችን ይዋዋላል፣የካሳ ክፍያ ይፈጽማል፣ ይስማማል፣ ያጸድቃል፤ ከኢንሹራንስ ካሣ ክፍያ ጋር በተያያዘ የሚረከባቸውን ማናቸውንም ጉዳት የደረሰባቸው ንብረቶችን ይሸጣል፣ ይለውጣል በውክልና ያስተላልፋል፣ ያስወግዳል፤

29.4.10. የአክሲዮን ማህበሩን የሥራ ዕቅድና በጀት፤ የረዥም ጊዜ ስትራቴጂና ፖሊሲዎች አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

29.4.11. ቦርድ ባፀደቃቸው ፖሊሲዎች መሠረት የሥራ መመሪያ፤ ፕሮሲጀር፣ ጋይድላይን እና ሌሎች የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ መቆጣጠሪያ ሠነዶች ያዘጋጃል፤ ያጸድቃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

29.4.12. የሥራ ድርሻን ኃላፊነት፣ሥልጣን እና የሥራ ክፍፍል የሚያሳይ የአክሲዮን ማህበሩን ድርጅታዊ መዋቅር /የኦርጋናይዜሽንናል ስትራክቸር/ አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

29.4.13. የዋና ሥራ አስፈፃሚ ምክትል የሆኑ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች /ሲነየር ኤክስኪዮቲብ ኦፊሰሮች/ ይመርጣል፤ ለቦርድ በማቅረብ ሹመታቸውን ያጸድቃል፤

29.4.14. የአክሲዮን ማኅበሩን የሂሳብ አያያዝ በሚመለከት አመራር ይሰጣል፣ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፤

29.4.15. የአክሲዮን ማኅበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ ለማከናወን መደበኛ የማኔጅመንት ስብሰባዎችን ያደርጋል፤

29.4.16. በሕጉ፣ በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና በባለአክሲዮኖች ጉባዔ በሚወሰነው መሠረት የተፈቀደለትን የመጠባበቂያ ሂሳብ እና ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሳቦችን ያቋቁማል፤ ያስተዳድራል፤

29.4.17. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ መሠረት የተሰጡትን ሥልጣኖች ለአክሲዮን ማኅበሩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

29.4.18. የአክሲዮን ማኅበሩን ጥቅም ለመጠበቅ ነገረ-ፈጅ ለመቅጠር/ለመወከል፣ ጠበቃ ለማቆም/ለመወከል፣ ሌሎች ወኪሎች ለመሾም እንዲሁም ሌሎች ባለሞያዎች ለመቅጠርና ለማሰናበት ሥልጣን ይኖረዋል፤

29.4.19. የሃዋላ ሰነዶችን፣ ቼኮችን፣ የምንዛሪ ሠነዶችን፣ የተስፋ ሠነዶችንና ሌሎች የማይተላለፉ ሠነዶችን ይፈርማል፣ ያጸድቃል፣ ቅናሽ ያደርጋል፤

29.4.20. አክሲዮን ማኅበሩን ከኪሳራ፤ ከጥፋት፣ ከድንገተኛ አደጋና ከማናቸውም ዓይነት ዕዳ ለመጠበቅ የሚያስችል የመድን ዋስትና ከታወቀ የመድን ኩባንያ ወይም ሰው ጋር ይዋዋላል፤

29.4.21. የባንክ የጊዜ ገደብ ተቀማጭን ሳይጨምር በዳይሬክተሮች ቦርድ ቅድሚያ ፍቃድ እና ከአክሲዮን ማኅበሩ ዓላማዎች ሳይወጣ በሥራ ላይ ያልዋለውን ገንዘብ ኢንቨስት ያደርጋል ወይም በአትራፊ ሥራ ላይ ያውላል፤

29.4.22. ዋና ሥራ አስፈፃሚው በቦርድ ከሚሰየሙት ኃላፊዎች በስተቀር በሕግ አግባብ ሠራተኛ የመቅጠር፣ የማሳደግ፣ ከደረጃ ዝቅ የማድረግና የማሰናበት ሥልጣን አለው፤

29.4.23. ሰራተኞች የረጅም ግዜ ብድር ሲወስዱ ውል ይፍርማል ኩባንያውን ወክሎ እንደአስፈላጊነቱ የመያዣ ውል ይዋዋላል ዋስትና ይቀበላል፤

29.4.24. የአክሲዮን ማኅበሩን ዓመታዊና ሌሎች መደበኛ የሥራ ክንውን ሪፖርቶች ወቅቱን ጠብቆ ለቦርዱና ለሚመለከታቸው ሁሉ ያቀርባል፤

29.4.25. በዚህ መመሥሪያ ጽሑፍ ውስጥ መደረግ ስለሚያስፈልጋቸው ማናቸውም ማሻሻያዎች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሃሳብ ያቀርባል፤

29.4.26. ለአክሲዮን ማኅበሩ የዕለት ተዕለት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ ወጪዎችና ክፍያችን ይፈቅዳል፤ ይፈጽማል፤

29.4.27. በቦርዱ ሰብሳቢ ሲጠየቅ ከማኅበሩ ጸሐፊ ጋር በመተባበር የቦርዱን ረቂቅ የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤

29.4.28. ከቦርዱ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር እና ከማኅበሩ ጸሐፊ ጋር በመተጋገዝ የቦርድ ስብሰባዎችን ዝግጅት ያስተባብራል፣

29.4.29. በዚህ መመሥሪያ ጽሑፍ ያልተጠቀሱ ነገር ግን ለአክሲዮን ማኅበሩ ዓላማዎች መሳካት አስፈላጊ የሆኑትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

29.4.30. እንደየሁኔታው በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤ የቦርዱንም ውሳኔዎች ያስፈፅማል፤

29.4.31. ዋና ስራ አስፈፃሚው ከላይ ከተሰጡት ሥልጣናት ውስጥ በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማህበሩ ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀጽ ሰላሳ፡
## የውጭ ኦዲተር/ሮች ስያሜ፤ ኃላፊነትና ተግባር

30.1. የአክሲዮን ማኅበሩ የውጭ ኦዲተር/ሮች በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይሰየማል፤

30.2. የውጭ ኦዲተሩ/ሮች የሥራ ዘመን የሦስት (3) ተከታታይ ዓመታት የሂሳብ ዘመን ይሆናል፤

30.3. የአክሲዮን ማኅበሩ የውጭ ኦዲተር/ሮች ተግባርና ኃላፊነት በንግድ ሕግ፣ በመድን ሥራ አዋጅ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ይፈፀማል፤

30.4. የውጭ ኦዲተር/ሮች ስለሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ፣ የሐብትና ዕዳ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ የንብረትና የሂሳብ መዛግብት እንዲሁም ሌሎች የፋይናንስ ሰነዶችን ትክክለኛነት መሠረታዊ የሂሳብ መርሆዎች እና አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት የመመርመርና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፤

30.5. የውጭ ኦዲተር/ሮች ሪፖርት ከአክሲዮን ማኅበሩ የበጀት ዓመት ማብቂያ በኋላ አግባብነት ባላቸው ሕጐች ላይ በተደነገገው መሠረት ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ይሰጣል።

## አንቀጽ ሰላሳ አንድ፡
## የማኅበሩ ጸሐፊ ሹመት፤ ሥልጣንና ተግባር

31.1. የማኅበሩ ጸሐፊ በዋና ሥራ አስፈፃሚው አቅራቢነት በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል፤ ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ይሆናል፤

31.2. የማኅበሩ ጸሐፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

31.2.1. የአክሲዮን ማኅበሩን መረጃዎችና መዛግብት የማደራጀትና የመያዝ፤

31.2.2. ለሚመለከተው አካል ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በወቅቱ የመስጠት፤

31.2.3. ለባለአክሲዮኖችና ለሦስተኛ ወገኖች መረጃ የመስጠት፤

31.2.4. የባለአክሲዮኖችና የቦርድ አባላትን ስብሰባዎች የማዘጋጀት፤

31.2.5. ቃለ-ጉባኤዎችን ማዘጋጀትና አደራጅቶ የመያዝ እና

31.2.6. በዋና ሥራ አስፈፃሚው እና በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን።

## አንቀጽ ሰላሳ ሁለት፡
## ስለአክሲዮን ማኅበሩ ሂሳብ አያያዝና ተዛማጅ ተግባራት
## ጠቅላላ ድንጋጌ

አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ውስጥ ስለሂሳብና መዝገብ አያያዝ የተደነገጉት ለአክሲዮን ማኅበሩ ሂሳብ አያያዝና አመዘጋገብ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ ሰላሳ ሶስት፡
## የፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች

33.1. አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የአክሲዮን ማኅበሩን የሥራ እንቅስቃሴ እና ያለውን የገንዘብ አቋም በግልጽና በትክክል የሚያስረዱ መዝገቦች በአግባቡ መያዝ አለባቸው፤

33.2. አክሲዮን ማኅበሩ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ዝርዝር ጉዳዩን ወዲያውኑ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፡-

33.2.1. ለመድን ገቢዎች ወይም ለሌሎች መድን ሰጪዎች/አበዳሪዎች ግዴታውን ለመፈፀም/ለመወጣት ያልቻለ ከሆነ፤

33.2.2. ለመድን ገቢዎች ወይም ሌሎች መድን ሰጪዎች/ አበዳሪዎች የሚያደርገውን ክፍያ ለማቋረጥ የተገደደ ሲሆን።

## አንቀጽ ሰላሳ አራት፡
## የማኅበሩ የሂሳብ ዓመትና ሪፖርት

34.1. የአክሲዮን ማኅበሩ የሂሳብ ዓመት እ.ኤ.አ ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዘመን ሰኔ 30 ያበቃል፤

34.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ በእያንዳንዱ የሂሳብ ዘመን ማብቂያ ላይ በዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚቀርብለትን ሪፖርት መነሻ በማድረግ የአክሲዮን ማኅበሩን አጠቃላይ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤

34.3. ሪፖርቱ ስለአክሲዮን ማኅበሩ ትርፍና ኪሳራ እንዲሁም ስለዳይሬክተሮችና ስለኦዲተሮች ክፍያ ዝርዝር መረጃ እንዲሁም ስለመጠባበቂያ ገንዘብ ምደባና ስለዘመኑ የትርፍ ድርሻ አመዳደብ ሃሳቦችን ያቀፈ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ አምስት፡
## የሂሳብ ሠነዶችን እና ሪፖርቶችን ስለመስጠት

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 427 መሠረት የአክሲዮን ማኅበሩ የንብረት ዝርዝር (Inventory)፣ የሀብት እና ዕዳ ሚዛን፣ የትርፍና የኪሳራ መግለጫ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ከመደረጉ ቢያንስ አርባ (40) ቀናት አስቀድሞ ለኦዲተር/ሮች እና ለሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መላክ አለበት፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ስድስት፡
## በጥሬ ገንዘብ ስለሚያዙ ሂሳቦችና የመጠባበቂያ ገንዘብ

አክሲዮን ማኅበሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የመቶኛ ስሌት መጠን ጥሬ ገንዘብ እና ጥሬ-ገንዘብ አከል የሆኑ ሠነዶችን /ሊኩይድ አሴት/ ይይዛል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ሰባት፡
## በቸልተኝነት ወይም እምነት ማጉደል ምክንያት ለሚደርሱ ኪሣራዎች የሚሸፈኑባቸው መጠባበቂያዎች

37.1. አክሲዮን ማኅበሩ በማናቸውም የወንጀል ድርጊት፣ ቸልተኝነት ወይም እምነት ማጉደል ምክንያት በአክሲዮን ማኅበሩ ላይ ለሚደርስ ኪሣራ መሸፈኛ የሚሆን መጠባበቂያ ገንዘብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስተያየት ይበቃል ተብሎ የሚታመንበትን መጠን ሂሳብ ሊይዝ ይችላል፤

37.2. ከእንደዚህ ዓይነቱ ኪሣራ ራሱን ለመጠበቅ አክሲዮን ማኅበሩ ተገቢ ፈቃድ ካለው ዕውቅ የመድን ድርጅት ዘንድ የመድን ዋስትና ሊገባ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ስምንት፡
## ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሳቦች

38.1. አክሲዮን ማኅበሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ የሚጠይቀውን በማሟላት ቀጥሎ የተመለከቱትን ወጪዎች የሚሸፍኑ የመጠባበቂያ ሂሳቦች ሊይዝ ይችላል።

38.1.1. የንብረት እርጅና ቅናሽ እና የተጠራቀመ የእርጅና ቅናሽ፣

38.1.2. በየዓመቱ ለተጠራቀሙ ኪሳራዎች መሸፈኛ፣

38.1.3. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ተፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ወጭ የሚሆን ሌላ መጠባበቂያ ሂሳብ መያዝ አለበት።

## አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ፡
## የትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል

39.1. በንግድ ሕጉ ከአንቀጽ 432 እስከ አንቀጽ 439 የተደነገጉት እና በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 37 ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የትርፍ ክፍፍሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያቀርበው ሃሳብ መሠረት የአክሲዮን ማኅበሩ ኦዲተር/ሮች ከመረመሩትና የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ካጸደቀው በኂላ ከተጣራ ትርፍ ላይ ታክስ፣ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ፣ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የተፈቀዱ ሌሎች የመጠባበቂያ ገንዘቦች፣ ያለፉት ኪሳራዎች እና ሌሎች ተቀናሾች ከተቀነሱ በኃላ በአንድ ጊዜ ክፍያ ተፈፃሚ ይሆናል፤

39.2. ትርፍ ለባለአክሲዮኖች በሚከፋፈልበት ጊዜ የሚከተሉት ሁለት ነገሮች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡-

39.2.1. ከተከፈለው ጠቅላላ ካፒታል ውስጥ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያለው የተከፈለ ካፒታል መጠን፣

39.2.2. በበጀት ዓመቱ ውስጥ የአክሲዮኖች ዋጋ በሙሉ ወይም በከፊል ተከፍሎ በአክሲዮን ማኅበሩ እጅ የቆየበት ጊዜ ናቸው።

39.3. የትርፍ ድርሻ የሚከፈልበት ቀንና ሁኔታ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል።

## አንቀጽ አርባ፡
## ካፒታል በሚቀነስበት ጊዜ የሚደረግ የትርፍ ክፍፍል ዕገዳ

የአክሲዮን ማኅበሩ ዋና ካፒታልና መጠባበቂያ ሂሳብ ከሚገባው በታች በሚቀንስበት ጊዜ ጉድለቱን ለማስወገድ የሚቻልበት እርምጃ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ውሳኔ መሠረት ከሚደረገው የገንዘብ ማዘዋወር በስተቀር፤ በዋናው ካፒታል ላይ የታየው ቅናሽ በሕጉ መሠረት ሙሉ በሙሉ እስኪተካ ድረስ አክሲዮን ማኅበሩ በማናቸውም ጊዜ ትርፉን አያሳውቅም ወይም አያከፋፍልም ወይም ከትርፍ ላይ ምንም ዓይነት የገንዘብ ዝውውር አይፈፅምም።

## አንቀጽ አርባ አንድ፡
## ስለምዝገባና ሪፖርቶችን ይፋ ስለማድረግ

41.1. በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የሚደረገው ማናቸውም ማሻሻያ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ከጸደቀ በኃላ አግባብ ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት ይመዘገባል፤

41.2. አክሲዮን ማኅበሩ በውጭ ኦዲተር/ሮች የተረጋገጠ የሐብትና ዕዳ ሚዛን፤ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰራጭ ጋዜጣ እንዲታተም ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ አርባ ሁለት፡
## የአክሲዮን ማኅበሩን ለማፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች እና አግባብነት ያላቸው ሥነ-ሥርዓቶች

42.1. የአክሲዮን ማህበሩ አግባብ ባለው ሕግ በተመለከተውና በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሠረት ሊፈርስ ይችላል፤

42.2. ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ ማናቸውም ቢሆን ለአክሲዮን ማኅበሩ መፍረስና ሂሳብ ማጣራት በቂ ሆኖ ይቆጠራል፤

42.2.1. የማኅበሩ ዓላማ ተግባራዊ ሳይሆን ሲቀር ወይም ማኅበሩ ተግባሩን ለማከናወን ከአቅሙ በላይ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥሙት፤

42.2.2. አክሲዮን ማኅበሩ በፈቃደኝነት እንዲፈርስ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን፤

42.2.3. ማናቸውም የጥቅም መብት ያለው ሰው በሚያቀርበው አቤቱታ መሠረት ፍርድ ቤት አክሲዮን ማኅበሩ የሚፈርስበት በቂ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ እንዲፈርስ ትዕዛዝ ሲሰጥ፤

42.2.4. አክሲዮን ማኅበሩ በመክሰሩ ምክንያት የዕዳ ማጣራትና የኪሳራ ፋይል በፍርድ ቤት ሲከፈት፤

42.2.5. ካፒታሉ በ3/4 (ሦስት አራተኛ) ሲቀንስ፤

42.3. አክሲዮን ማኅበሩ እንዲፈርስ ጠቅላላ ጉባዔው ሲወስን ሂሳብ አጣሪዎችን ይሾማል፤

42.4. ማንኛውም የአክሲዮን ማኅበሩ አባልም ሆነ ኦዲተር/ሮች የሂሳብ አጣሪዎችን ሹመት በመቃወም ያመለከተ እንደሆነ የቀረበው መቃወሚያ በቂ ምክንያት ያለው ሆኖ ካገኙት ጠቅላላ ጉባዔው ሹመቱን ሊሽረው ወይም ሊያስቀረው ይችላል፤

42.5. ስለማህበሩ መፍረስ የተሾሙት ሂሳብ አጣሪዎች ተግባራቸውን አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎች መሰረት የሚያከናውኑ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አርባ ሶስት፡
## አክሲዮን ማኅበሩ በሥራ የሚቆይበት ጊዜ

አክሲዮን ማኅበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

## አንቀጽ አርባ አራት፡
## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

44.1. በሥራ ላይ የነበረው የአክሲዮን ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተሻረ ሲሆን በሥራ ላይ የነበረው የአክሲዮን ማኅበሩ የመመሥረቻ ፅሑፍ በዚህ መመሥረቻ ፅሑፍ ተሻሽሏል፤

44.2. ይህ የመመሥረቻ ጽሑፍ በማናቸውም ጊዜ በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሻል ይችላል፤

44.3. በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና አግባብነት ባላቸው አስገዳጅ ሕጎች መካከል መቃረን ሲኖር አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ውስጥ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ በንግድ ሕጉና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉትን በመከተል ይተገበራል፤

44.4. በዚህ የመመሥረቻ ጸሑፍ የአማርኛው ቅጂና የእንግሊዘኛው ቅጂ መካከል የትርጉም ልዩነት የተፈጠረ እንደሆነ የአማርኛው ቅጂ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ይህ መመሥረቻ ጽሑፍ በባለአክሲዮኖች 23ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ከጸደቀ በኋላ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ሲያገኝ እና በሚመለከተው አካል ሲመዘገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ህዳር 17 ቀን 2017 ዓም አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፡፡**

**የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እንዲሁም የማህበሩ ጸሐፊ ሥም እና ፊርማ፤**

| ተ.ቁ | ስም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1. | ዶ/ር ሳራ ሱሩር መሐመድ | ሰብሳቢ | |
| 2. | ዳሸን ባንክ አ.ማ. በዋና ስራ አስፈጻሚው በአቶ አስፋው ዓለሙ አማካኝነት | አባል | |
| 3. | አቶ ዮናስ ዱጉማ ሁንዴ | አባል | |
| 4. | አቶ ሁሴን አህመድ ሀሰን | አባል | |
| 5. | አቶ ሰለሞን በዳኔ ጉራሮ | አባል | |
| 6. | ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር በአቶ አያሌው ይማም እሸቴ አማካኝነት | አባል | |
| 7. | አቶ ጣሂር መሐመድ ቲጃን | አባል | |
| 8. | ካቤ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር በአቶ ሁሴን ሰዒድ አሊ አማካኝነት | አባል | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9. | ወ/ሮ ምንትዋብ አበበ አውራሪስ | አባል | |
| 10. | አቶ አቢይ ወረደ ቂርቆስ | የማህበሩ ፀሀፊ | |